# ይለቀስ ለባንዳ

በፍቅር በአንድነት
በሰላም እርሻ ላይ
ዲሞክራሲ አብቦ
ጐምርቶ እንዲታይ
ለአገር ስትሉ
ለሕዝብ ስትሉ
ያላችሁ በስቃይ
እንደ ስንዴ ቅንጣት
ምርጥ ዘር በመሆን
ሚሊዮን ያፈራችሁ
ብትሞቱ አናለቅስም
እናንተ ህያው ናችሁ።
እስርም ቢያገኛችሁ
አሳሪው ተሞኘ
ስጋችሁን እንጂ
መንፈስ አላገኘ።
በቅንጅት መንፈስ
መሰረት ተጥሎ
መንገዱ ተጠርጓል
የግዜ ጉዳይ ነው
ዲሞክራሲ ያብባል
አሳሪው ታሳሪው
ሁሉም ነጻ ይወጣል።
የመንፈሱ ችቦ
ሀይሉ ብርሀኑ
ይብስ ተንቦግቡጐ
ያጠፋል ድቅድቁን
ጨለማን ጠራርጐ
ለወገን መጥበሻ
በመሆን ማገዶ
ለወያኔ ያደረ
ሆኖ ባህር ማዶ
ህዝቡን እያስራበ
እሱ ለማግሳት
ለወያኔ ያደረ
ቁጭ ብሎ አገር ቤት።
ከወያኔ ጋራ
ከራስ በላይ ንፋስ
ብሎ እየዘመረ
ብርሀን ፈንጥቆለት
ጨለማ ያፈቀረ
እሱ ነው የሞተ
እሱ ነው የታሰረ።
ለእናንተ አናለቅስም
የስንዴ ቅንጣቶች
በወህኒ ያላችሁ
ሲቪክ ማህበራት
ቅንጅት መሪዎች
የህዝብ አንደበቱ
ነጻ ጋዜጠኞች
ሚሊዮን አፍርቷል
ድንቅ ተጋድሏችሁ
በሞትና በእስር
ማ ሊያሸንፋችሁ
ለእናንተ አናለቅስም
የኢትዮጵያ ትንሳኤ
እናንተ ህያው ናችሁ።
ይልቅስ ይለቀስ
ይመታ ደረት
በመንፈስ በስጋ
መርጦ ባርነት
ከወያኔ ጋራ
ከራስ በላይ ንፋስ
ብሎ እየዘመረ
ለስጋው ሲዳክር
መንፈሱን ላሰረ
አገርና ህዝቡን
ለስጋው ለከዳ
ይመታለት ደረት
ይለቀስ ለባንዳ።
እሱ ነው የሞተ
እሱ ነው የታሰረ
ብርሀን ፈንጥቆለት
ጨለማ ያፈቀረ።

ስሜነህ መሸሻ
ከላስ ቬጋስ